COMMONWEALTH of VIRGINIA
**Virginia Employment Commission**
First Level Appeals, P.O. Box 26441, Richmond, Virginia 23261-6441
804-786-3020 · 800-552-4500 · ፋክስ 804-786-8492

# የይግባኝ ማስታወቂያ

A-FLA-001

SSN:
መዝገብ:

በአቤቱታ አቅራቢ የቀረበውን የስራ ቅጥር የይገባኛል ጥያቄ አስመልክቶ ከተላለፈው የምክትል ውሳኔ በመነሳት ይግባኝ ቀርቧል። ይግባኙ ቀን <የመዝገብ ቀን> የተጻፈበት ሲሆን አስመዝጋቢው <የይግባኝ ባይ አይነት> ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰማው ችሎት ቀጠሮ ይያዝለት እና የችሎቱን ቀንና ሰዐት የሚገልጽ መደበኛ ማስታወቂያ ይሰጥዎታል። ከዚህ ቢሮ ጋር ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት ከላይ የተገለጸውን የመዝገብ ቁጥር ይጥቀሱ።

ችሎቱ በገለልተኛ የይህባኝ መርማሪ አማካኝነት ይካሄዳል። የችሎቱ አላማ ከተከራካሪ ወገኖች በይግባኙ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን በተመለከተ ማስረጃ ለመውሰድ ነው። እያንዳንዱ ወገን የመመስከር፣ በአካል የመቅረብና ምስክሮችን ጥያቄዎች የመጠየቅ፣ እና ማሳያዎችን የማቅረብ መብት አለው። የይግባኝ መርማሪው መኃላ ይቀበላል፣ ችሎቱን ይቆጣጠራል እንዲሁም ማሳያዎችን ተቀብሎ በመዝገብ ያሰፍራል። ህጉ ችሎቱ በይግባኝ መርማሪው እንዲመዘገብ ያስገድዳል። ሁሉም ምስክርነቶች በመኃላ ወይም በማረጋገጫ መሰጠት አለባቸው።

አቤቱታ አቅራቢው እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች የማግኘት ብቁነት ከሳምንት ሳምንት መነሻነት ላይ እንደሚመሰረት ማወቅ አለበት። ይግባኙ በይደር ተይዞ በሚቆይበት ወቅት ቀጣይነት ያለው የጥቅማ ጥቅሞች መብትዎን ለማስከበር እንዲቻል ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችዎን ማስመዝገብዎን መቀጠልዎ አስፈላጊ ነው። የይገባኛል ጥያቄዎችዎን በአግባቡ አለማስመዝገብ ጥቅማ ጥቅሞችዎን እንዲከለከሉ ሊያደርግ ይችላል። አቤቱታ አቅራቢው ሙሉ በሙሉ በተቀየረ ውሳኔ ምክንያት ክፍያዎችን የሚያገኝ ከሆነ የጥቅማ ጥቅሞች መልሶ ክፍያ መክፈል ያስፈልጋል።

ይህ የይግባኝ ማስታወቂያ በ<የመልእክት ቀን> ተልኳል።

የኮሚሽኑ ችሎት ፀሀፊ

**እያንዳንዱን ወገን የተመለከተውን ጠቃሚ መረጃ ከጀርባ ጎኑ ላይ ያንብቡ።**

## ጠቃሚ መልዕክት – ሁሉንም መመሪያዎች አንብበው ይከተሉ

**በችሎቱ ላይ ተሳታፊ መሆን አለብዎት**: ይህ ማስረጃ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ብቸኛው ችሎት ሊሆን ይችላል። ተጨማሪ ይግባኞች የሚኖሩ ከሆነ ይግባኞቹ በዚህ ችሎት መዝገብ ላይ የገባ ማስረጃ ምርመራ ብቻ ሊሆን ይችላል። በችሎቱ ላይ የማይሳተፉ ከሆነ የይግባኝ መርማሪው በጉዳዩ ላይ በቀረበለት ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ያሳልፋል።

**መወከል**: ጉዳይዎን እራስዎ ሊያቀርቡ ይችላሉ፣ ወይም በጠበቃ ወይም ሌላ ሰው ሊወከሉ ይችላሉ። ቢወከሉም እንኳን በችሎቱ ላይ መገኘት አለብዎት። የጠበቃዎን/ተወካይዎን ክፍያዎች መክፈል አለብዎ፤ ሆኖም ለአቤቱታ አቅራቢው የሚከፈሉ የትኛውም ክፍያዎች በኮሚሽ መፈቀድ አለበት። በማህበረሰብዎ ውስጥ ካለው የህግ እርዳታ/ድጋፍ ማህበር ጋር በስልክ ቁጥር 1-866-534-5243 በመነጋገር ነጻ የህግ አገልግሎቶችን ሊያገኙ ይችላሉ። በተጨማሪም የቨርጂኒያ ግዛት መስመርን የህግ ባለሙያ ሪፈራል አገልግሎት በስልክ ቁጥር 1-800-552-7977 ደውለው በማነጋገር ጠበቃ ሊያገኙ ይችላሉ። ሌላ ሰው እንዲወከልዎ የሚያደርጉ ከሆነ የሚወክልዎን ሰsው ስም፣ አድራሻና ስልክ ቁጥር በአስቸኳይ ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ አለብዎት።

**ምስክሮች/ቃለ መኃላዎች**: እርስዎን ወክሎ የሚመሰክርልዎት ምስክር ማሰማት የሚፈሎጉ ከሆነ ምስክርዎ ችሎቱ ላይ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለብዎ። መጥሪያ መስጠት አስፈላጊ ከሆነ ይህን ወዲያውኑ ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ ያሳውቁ እና ጥያቄዎ ይታያል። መጥሪያ የሚሰጠውን ሰው ስምና አድራሻ ማቅረብ አለብዎ። እርስዎ እና/ወይም ምስክርዎ መገኘት የማትችሉ ከሆነ ሁሉንም ተገቢ ማስረጃዎች በተቻለ መጠን በቅደም ተከተላቸው መሰረት ቢሆን ይመረጣል የሚዘረዝር ቃለ መኃላ (በክብር መዝገብ ሹም ፊት መሃላ የተፈፀመበት መግለጫ) ማስገባት አለብዎ። ቃለ መኃላዎች በችሎቱ ወቅት በመኃላ ከሚሰጥ ምስክርነት እኩል ሚዛን ላይደፉ ይችላል። ቃለ መኃላውን ከችሎቱ ቀን በፊት ለይግባኝ መርማሪው እና ለየትኛውም ተቃራኒ ወገን እንዲደርስ ለማስቻል በወቅቱ ያስገቡ። የምስክር በችሎቱ ላይ አለመገኘት ችሎቱን ለማስተላለፍ ወይም ለመቀጠል አሳማኝ ምክንያት ላይሆን ይችላል።

**ማስረጃ**: በችሎቱ ላይ በሚሳተፉበት ወቅት ለጉዳይዎ የሚያቀርቡትን ማንኛውንም ያሉዎትን ነገር ይዘው ይቅረቡ። ይህ ከብዙ በጥቂቱ የአሰሪ ህጎች፣ ደብዳቤዎች፣ የዶክተር መግለጫዎች፣ የቼክ ጉራጆች፣ ውሎች እና የሰአት መቆጣጠሪያ መዝገቦች ሊሆን ይችላል። በችሎቱ ላይ እንደሚጠቀሟቸው ያቀዷቸውን ሰነዶች ኮፒዎች በአስቸኳይ ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ እና ለሁሉም ተቃራኒ ወገኖች መላክ አለብዎ።

**አስተርጓሚዎች**: አስተርጓሚ የሚፈልጉ ከሆነ ይህን ወዲያውኑ ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ አለብዎት።

**ማስተላለፍ**: ማስተላለፎች ሊፈቀዱ የሚችሉት ጥያቄውን መከልከል ቁሳዊና ከባድ ጉዳት እንደሚያደርስ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው። የግድ ማስተላለፊያ መጠየቅ የሚኖርብዎ ከሆነ ይህን ወዲያውኑ በስልክ ቁጥር 804-786-3020 ወይም 800-552-4500 ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ አለብዎት። የማስተላለፍ ጥያቄዎ የሚከለከል ከሆነ በችሎቱ ላይ ከሚቀርበው ማስረጃና ምስክርነት በመነሳት ውሳኔ ይተላለፋል። የማስተላለፊያ ጥያቄዎ ስለመፈቀዱ የማይነገርዎ ከሆነ በችሎቱ ላይ መገኘት አለብዎ።

**መውጣት**: ይግባኙን የሚያስመዘግበው ወገን በየትኛውም ጊዜ ከይግባኙ ለመውጣት ሊጠይቅ ይችላል። የመውጫ ጥያቄው በጽሁፍ መቅረብ እና በይግባኝ ባዩ መፈረም እንዲሁም ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ መቅረብ አለበት።

**የመልዕክት አድራሻ**: የትኛውንም የአድራሻ ለውጥ የሚያደርጉ ከሆነ ይህን ወዲያውኑ ለኮሚሽኑ የችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ አለብዎ። ይህ የሚቀይረው የዚህ ይግባኝ አድራሻዎን ብቻ ነው። ለዩኤስ የፖስታ አገልግሎት የማስተላለፊያ ትእዛዝ ማስመዝገብ ለኮሚሽኑ ተገቢ ማስታወቂያ እንደመስጠት አያስቆጥርም። የአድራሻ ለውጡን በቀጥታ ለኮሚሽኑ ባለማሳወቅዎ ምክንያት ብቻ ችሎት ወይም የማስመዝገቢያ ማብቂያ ጊዜ የሚያልፍዎ ከሆነ ችሎቱ በድጋሚ ቀጠሮ አይያዝለትም እንዲሁም የማስመዝገቢያ ማብቂያ ጊዜው አይራዘምም።

**የዚህን ችሎት ሥነ ሥርአት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ካስፈለግዎት ሳይዘገዩ በ፡**
**First Level Appeals, P.O. Box 26441, Richmond, Virginia 23261-6441**
**804-786-3020 · 800-552-4500 · ፋክስ 804-786-8492**
**የሚገኘውን የኮሚሽኑን ችሎት መዝጋቢ ያነጋግሩ**

ይህ የይግባኝ ማስታወቂያ ዛሬ በ[ቀን] ለሚከተለው አካል ተልኳል: